# እድሜ ጠገቧ አያቴ



14-17ኛው ሳምንት

2ኛ ክፍል

መጽሐፍ 11

# እድሜ ጠገቧ አያቴ

መጽሐፍ 11 | 2ኛ ክፍል | 14-17ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ::

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



አያቴ ሰማንያ አመቷ ነው::
የሰውነቷ ቆዳ ተሸብሽቧል::
ቢሆንም የደስደስ አላት::
ከእኛ ጋር ትኖራለች::



ጧት ጧት በረንዳ ላይ ተቀምጣ ፀሐይ መሞቅ ትወዳለች። እኔም ከእሷ ጎን እቀመጣለሁ። ተረት ስትተርትልኝ በጣም ደስ ይለኛል። አያቴን በጣም እወዳታለሁ።

የምትፈልገውን ሁሉ ለማማሟላት እጥራለሁ። እጇንና ፊቷን አስታጥባታለሁ። የዝንብ መከላከያ ጭራዋን አቀብላታለሁ። ልብሷ ሲጎተትባት እሰበስብላታለሁ። ምርኩዟ ሲወድቅባት አንስቼ እሰጣታለሁ።



ሁሌም ከአሏጋር መሆን ያስደስተኛል:: ከቦታ ቦታ ስትዘዋወር አብሬያት እሆናለሁ::

አያቴ በትምህርቴ እንድጎብዝ አድርጋኛለች:: ዘወትር በዕቅድ እንድመራ ትመክረናለች:: ጠንክሬ እንድማር ታበረታታኛለች:: እኔም ምክሯን አክብሬ እማራለሁ:: ዘወትር አጠናለሁ:: ሲደክመኝ ተረት ተርቾልኝ እላታለሁ::

በየጊዜው አዳዲስ ተረቶች ትተርትልኛለች። ተረቷ ምንጊዜም አይሰለቸኝም።



የቤት ሥራ ሲሰጠኝ ከከበደኝ አያቴን እጠይቃታለሁ፡፡ ካወቀችው ታስረዳኛለች፡፡ ካላወቀችው ሌሎችን ጠይቄ እንድረዳ ትመክረኛለች፡፡ ከትምህርት ውጪም ጥያቄ እጠይቃታለሁ፡፡

አንድ ቀን “በዓለም አንደኛው ሀብታም ማን ነው?” ብዬ ጠየቅኋት:: ከትከት ብላ ሳቀች:: እኔም አብሬ ሳቅሁ::



አያቴ ሳቋን አቋርጣ “በዓለም አንደኛው ሀብታም ጤነኛ ሰው ነው::”

“እንዴት?” አልኳት:: “ጤነኛ ሰው ሠርቶ ሀብት ማግኘት ይችላል” አለችኝ::

“ደሀውስ ማን ነው?” አልኳት። “ደሀውማ ሥራ የማይወድ ሰው ነው። ሥራ የማይወድ ሰው ሀብታም አይሆንም” አለችኝ። እኔም በአያቴ መልስ በጣም ተገረምኩ።

USAID

ከአሜሪካን ህዝብ